2. አመልካች በወንጀል ሕግ ቁጥር 543 ጥፋተኛ ናቸው ተብሎ የተሰጠው የጥፋተኛነት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
3. አመልካች የወንጀል ሕግ ቁጥር 567"ን" በመተላለፍ በፈፀሙት በልማዳዊ ድርጊት ጉዳት ማድረስ ወንጀል የተሰጠው የጥፋተኛነት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ አመልካች በዚህ ድንጋጌ ጥፋተኛ ስለተባሉ በሁለት አመት ቀላል እስራት እንዲቀጡ የተሰጠውም የቅጣት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
4. አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ድርጊት የሚያስቀጣው በቀላል እስራት ወይም በአማራጭ በገንዘብ መቀጮ በመሆኑ አመልካች ብር 300.00 እንዲቀጡ የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 46189

ሚያዝያ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ኂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ዓብዱራሂም አህመድ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ሐረገወይን ተፈራ - ጠበቃ ጥበቡ ምህረቴ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ ወርቁ ገመቹ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው ጉዳይ የወንጀል ሲሆን አመልካች በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት በጠበቃቸው አማካኝነት ግንቦት 24 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ጥቅምት 25 በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

ይህ ችሎትም የአመልካች አቤቱታ፣ ከበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች እንዲሁም አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች የተከሰሱት፡- በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወ/መ/ሕ/ቁ. 32(1(ሀ) እና (ለ)) እና 692/1/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ የማይገባቸውን ብልጽግና ለማግኘት አስቀድሞ በማሰብ ክሱ በስር ፍርድ ቤት ከተቋረጠው ከአቶ ዘላለም ተስፋዬን የሲሊጥ ነጋዴና አቅራቢ በማስመሰል ለግል ተበዳይ ሽቶ በቀለ ካስተዋወቀች በኋላ የግል ተበዳይን በማሳመን ወደ ተሳሳተ እምነት በመምራት ግንቦት 21 ቀን 1998 ዓ.ም ከቀኑ በግምት 5፡30 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15 ክልል ውስጥ ልዩ ቦታው ከኢምፔሪያል ሆቴል በስተጀርባ ከሚገኘው የግል ተበዳይ ድርጅት በሆነው ፐርፍ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ግቢ ውስጥ ክስ የተቋረጠበት ግለሰብ ለድርጅቱ ብዛቱ 6000(ስድስት ሺህ) ኩንታል ሲሊጥ በብር 3,618,000(ሶስት ሚሊዮን ስድስት መቶ አስራ ስምንት ሺህ ብር) ለማቅረብ ከተነጋገሩ በኋላ የቅድሚያ ክፍያ ያስፈልገኛል በማለት በእለቱ ብር 500,000(አምስት መቶ ሺህ) የያዘ ቼክ በመቀበል እንዲሁም ግንቦት 24 ቀን 1998 ዓ.ም ብር 50,000(አምሳ ሺህ ብር) ጉንደር ከሚገኘው የአቢሲኒያ ባንክ እንዲቀበል በአቶ

ያለው በቀለ ስም ተልኮለት በአጠቃላይ ብር 550,000(አምስት መቶ አምሳ ሺህ ብር) ወጪ አድርጐ ከወሰደ በኋላ ገንዘቡን ይዞ በመሰወሩ ሁለቱም የማታለል ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ አመልካች በክሱ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ የድርጊት አፈፃፀሙን በመካዳቸው አቃቤ ሕጉ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች ለማስረጃነት አቅርቦ አመልካች ክሱን እንዲከላከሉ ተደርጐ የወንጀሉ ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜና ቦታ ተገኝተው በሰሊጥ ውሉ ላይ በእማኝነት መፈረማቸውን በጭብጥነት አሲይዘው የሰነድና የሰው ማስረጃዎችን አቅርበዋል፣ አሰምተዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም አመልካችን በመከላከያ ማስረጃ በሰሊጥ ውሉ ላይ በእማኝነት ስለመፈረማቸው እና የግል ተበዳይም በአቶ ዘላለም ተስፋዬ የፍትሐብሔር ክስ አቅርበው ገንዘቡ እንዲመለስላቸው ማስፈረዳቸው ቢረጋገጥም የግል ተበዳይን ወደ ስህተት እንዲመሩ አላደረጉም ለማለት የሚያስችል አይደለም በማለት በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቀሶ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጐ በአንድ ዓመት ቀላል አስራት እንዲቀጡ እና የቅጣቱ አፈፃፀም በሦስት አመት ገደብ እንዲሆን ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡

የአመልካች በዚህ ችሎት ባቀረቡት ክርክር በአመልካች በኩል የተፈፀመው ድርጊት የማታለል ወንጀልን የሚያቋቁም አይደለም በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በአንፃሩ ድርጊቱ የማታለል ወንጀልን የሚያቋቁም ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ይህ ችሎትም በአመልካች ላይ የቀረበው የወንጀል ክስ የማታለል ወንጀልን ያቋቁማል ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ይዞ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 692/1/ መሰረት ተጠያቂ የሚሆነው የማይገባ ብልጽግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለጽ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው አታልሎ የራሱን ወይም የሦስትኛ ወገንን የንብረት ጥቅም የሚጐዳ አድራጐት እንዲፈፀም ያደረገ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ እንግዲህ አንድ ሰው የወንጀል ተጠያቂነት የሚኖርበት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2/ ስር እንደተመለከተው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ፈፀሙ የተባለው ክሱ የተቋረጠውን አቶ ዘላለም ተስፋዬን የሰሊጥ ነጋዴና አቅራቢ በማስመሰል ለግል ተበዳይ ለአቶ ሹቶ በቀለ አስተዋውቀው የግል ተበዳይ ገንዘብ ላይ ጉዳት አድርሰዋል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አቶ ዘላለም ተስፋዬ የሰሊጥ ነጋዴ አለመሆናቸው ካለመረጋገጡም በላይ አመልካች ይህንኑ እያወቁ ለግል ተበዳይ የተሳሳተ ነገር እውነት አስመስለው የተናገሩበት ሁኔታ ስለመኖሩ አልተረጋገጠም፡፡ ይልቁንም አቃቤ ሕጉ የሰሊጥ ነጋዴ ሳይሆኑ ነጋዴ ናቸው የተባሉትን ግለሰብ በተመለከተ ክሱን ያቋረጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የግል ተበዳይም ከአቶ ዘላለም ተስፋዬ ጋር የነበራቸው ግንኙነት ፍትሐብሔራዊ የነበረ ስለመሆኑ ተረጋግጦ በፍትሐብሔር ችሎት ውሳኔ ተሰጥቶ ገንዘባቸው እንዲከፈላቸው ተወስኗል፡፡ ይህ ሁሉ የሚያሳየው አመልካች የማታለል ተግባር አለመፈፀማቸውን ነው፡፡ በመሆኑም የአመልካች ተግባር የማታለል ተግባርን የሚያቋቁም ባለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 23/2/ እና 692/1/"ን" ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 54121 ጥቅምት 25 እና ኀዳር 04 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጠቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 42198 የካቲት 25 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ለ/2/ መሰረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ተግባር የማታለል ወንጀልን የሚያቋቁም አይደለም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ